GEORGETOWN
Wet Weather Treatment Station

King County
Protecting Our Waters
Doing our part on rainy days

# የዱዋሚሽ ንጽህና ለመጠበቅ በመስራት ላይ

በጆርጅታውን እና ሌሎች የኪንግ ካውንቲ ክፍሎች፣ ከቤቶች የሚወገዱ ቆሻሻ ፈሳሾች እና ጎርፍ ውስጥ ለውስጥ በተዘረጉ ትቦዎች አማካኝነት ወደ ዌስት ፖይንት የፍሳሽ ማጣሪያ ማእከል በማጓጓዝ እንዲጣሩ ይደረጋል። ትቦዎቹ እና የማጣሪያ ማእከሉ ጤንነታችን እንዲጠበቅ እንዲሁም ንጽህናቸው የተጠበቁ ወንዞች፣ ሀይቆች፣ እና ፒዩጌት ሳውንድ እንዲኖሩን ይረዳል።

ከባድ ጎርፎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ፣ ከፍሳሽ ማስወገጃ ስርአቱ አቅም በላይ የሆነ ብዛት ያለው የዝናብ ውሃ ወደ ትቦዎቹ ይገባል። በአሁኑ ጊዜ፣ ጆርጅታውን ላይ፣ ከመጠን በላይ የሆነ ውሃ ከቆሻሻ ፍሳሽ ጋር ተቀላቅሎ ሳይጣራ ወደ ዱዋሚሽ ወንዝ እየተለቀቀ ይገኛል። ይህ ከልክ ያለፈ የተዋሀደ ፍሳሽ ፍሰት፣ ወይንም CSO እንለዋን። CSOs ለፍሳሽ ማስወገጃ ስርአቱ አስፈላጊ የሆኑ የደህንነት የፍሳሽ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ናቸው። ከቤታችን እና ከመንገዶች ሊመጡ የሚችሉ ተጨማሪ ፍሳሾችን ይከላከላሉ። ይሁን እንጂ፣ CSOs በአካባቢ እና በማህበረሰቡ ጤና ላይ ጉዳት ያስከትላሉ። ኪንግ ካውንቲ በአካባቢያችን ወደሚገኙ የውሀ አካሎች የሚገቡ የ CSOs ቁጥሮችን ለመቀነስ እየሰራ ይገኛል።




ጆርጅታውን ላይ፣ ኪንግ ካውንቲ ዱዋሚሽ ወንዝን ከ CSOs ለመከላከል የሚያስችል የእርጥበታማ የአየር ሁኔታ ማጣሪያ ጣብያ ይገነባል። በከባድ ዝንብ ወቅት ከባድ ጎርፎች ሲከሰቱ፣ ከመጠን ያለፈው ቆሻሻ ፍሳሽ እና ጎርፍ ወደ ዱዋሚሽ ወንዝ ከመግባታቸው በፊት በአዲሱ ጣብያ ይጣራሉ። አዲሱ ጣብያ ወደ ዱዋሚሽ ወንዝ ሳይጣራ የሚገባ ቆሻሻ ውሀ መጠን በ95 በመቶ ይቀንሰዋል።

GEORGETOWN
Wet Weather Treatment Station

King County
Protecting Our Waters
Doing our part on rainy days

# ለማጣሪያ ጣቢያው የተመረጠ ቦታ

በቅርብ ጊዜ ኪንግ ካውንቲ ለጆርጅታውን እርጥበታማ የአየርሁኔታ ማጣሪያ ጣብያ የሚሆን ቦታ መርጧል (ካርታ ይመልከቱ)። ቦታው በደቡባዊ ሚቺጋን ጎዳና በ East Marginal Way South እና Fourth Avenue South መካከል ይገኛል። ሳይቱ ብዙ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት በጥንቃቄ ነው የተመረጠው።




• በፍሳሽ ማስወገጃ ትቦዎች አጠገብ ነው የሚገኘው።

• ወደ ዱዋሚሽ ወንዝ ቅርብ መሆኑ እና አዲስ የተጣራ ፍሳሽ የሚለቀቅበት ግንባታ የሚኖርበት በመሆኑ።

• ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ ስርአቱ እና ወደ ወንዙ ቅርብ በመሆኑ ምክንያት የሚዘረጉ አዳዲስ ትቦዎችን መጠን ይቀንሳል። ይህ የግንባታ ጊዜ ያሳጥራል እንዲሁም የመንገድ ማስተጓጎልን ይቀንሳል።

ለማጣሪያ ጣብያው የሚያስፈልገው ቦታ በእጁ ለማስገባት ኪንግ ካውንቲ አራት የባለንብረቶች ይዞታዎችን በግዢ መልክ ይረከባል። የካውንቲው ሪልኢስቴት ቡድን የካውንቲው ፖሊሲ እና የስቴት ህግ ላይ በመመስረት ለባለንብረቶችን ፍላጎቶች እና ሀሳቦች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ከእያንዳንዱ ባለንብረት ጋር በቅርበት እየሰራ ይገኛል።

# የፕሮጀክቱ የጊዜ ሰሌዳ

ጣብያው አሁን በንድፍ ስራ ሂደት ላይ ይገኛል። የፕሮጀክቱ ቡድን ውሀ ለማጣራት ስለሚያስፈልገው መሳሪያ እና ህንጻው ቦታው ላይ እንዴት መቆም እንዳለበት በተመለከተ ውሳኔዎችን አሳልፏል። የንድፍ ስራው 2017 መጀመሪያ ይጠናቀቃል ብለን እንጠብቃለን።

ስለፕሮጀክቱ ተጨማሪ ማወቅ የሚፈልጉት ነገር ካለ፣ ወይንም ማጋራት የሚፈልጉት ሀሳብ ካለዎት፣ Kristine.cramer@kingcounty.gov ወይንም 206-477-5415 በመጠቀም ከክሪስቲን ክራመር ጋር ይገናኙ። በስልክዎ አማካኝነት መልእክት ይተዉ እና ቋንቋዎን ያሳውቁ፣ ወይንም የሚናገሩት ቋንቋ ምን እንደሆነ ለክሪስቲን ይንገሯት። አስተርጓሚ ያለ ምንም ክፍያ ይቀርብልዎታል።